አፍሪካ ቲቪ

1

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት “የልብ ተግባራት”

3

በቴሌግራም

# አፍሪካ አካዳሚ
## AFRICA ACADEMY

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

# የልብ ተግባራት

አላህ ልብን ንጉስ አድርጎ ፈጠረና ሌሎች አካላትን የሱ ሰራዊት አደረጋቸው፡፡ንጉሱ ካማረ ሰራዊቱም ማማሩ አይቀርም፡፡

- ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «በየአካላችን ውስጥ አንዲት ልማጭ (ቁራጭ) ስጋ አለች፡፡ እሷ ካማረች አካላችን ሁሉ ያምራል፡፡ እሷ ከተበላሸች አካላችን ሁሉ ይበላሻል፡፡ እሷም ልብ ናት» ብለዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ልብ የእምነትና የአላህ ፍራቻ ወይም የክህደት የንፍቅናና የሺርክ ቦታ ነው፡፡
- ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ወደ ልባቸው እያመለከቱ)

‹‹ተቅዋ (የአላህ ፍራቻ) ቦታው እዚህ ውስጥ ነው›› ብለዋል፡፡

- ኢማን ማለት በውስጥ የሚታመን፤ በአንደበት የሚነገርና በአካል የሚተገበር ነው፡፡ እናም ልብ ከውስጥ አረጋግጦ ያምናል፡፡ ከዚያም የምስክርነት ቃሉን ምላስ እንዲናገር ያደርጋል፡፡
- ከዚያም ልብ ውስጣዊ ስራውን ማለትም አላህን ማፍቀር፤ እሱኑ መፍራት፤ ከሱ ተስፋ ማድረግንና የመሳሰሉትን ውስጣዊ ተግባራት ያከናውናል፡፡ ምላስ በዚክር እና በቁርአን ይንቀሳቀሳል፡፡ አካላት በሩኩዕ፤ በሱጁድና በሌሎችም ውጫዊ መልካም ተግባራት ይውላሉ፡፡ አካል ሁልጊዜም የልብ ተከታይ ነው፡፡ በልብ ያለ ነገር ሁሉ በሆነ ነገር ላይም ቢሆን በአካል ላይ በግልፅ መንፀባረቁ አይቀርም፡፡

- የልብ ተግባራት የሆኑ ነገሮች ሁሉ ተቃራኒዎቻቸው የልብ በሺታዎች ናቸው፡፡
- ለምሳሌ የፍፁምነት ተቃራኒው ይዩልኝ (ልታይባይነት) ነው፡፡ የእርግጠኝነት ተቃራኒው መጠራጠር ነው፡፡
- የውዴታ ተቃራኒው ጥላቻ ነው፤ ወ.ዘ.ተ፡፡
- ልቦቻችንን ችላ ካልናቸውና መንከባከብ ከተውናቸው ወንጀሎች ይረባረቡባቸውና ድራሻቸውን ያጠፏቸዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ነብዩ ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ እንዲህ ብለዋል፡
- ‹‹የሰው ልጅ አንዲት ስህተት ሲፈፀም በልቡ ላይ ነጥብ ትቀመጣለች፡፡ ከዚያም ወደ አላህ ከተመለሰና የአላህን ምህረት ከጠየቀ ትፀዳለች፡፡ ከደገመ ግን ይጨምርበታል፡፡ ከዚያም ከደጋገመው ነጥብም ይጨምርበታል፡፡ ይኼው ሂደት እሷ እስከምትቆጣጣረው ድረስ ይቀጥላል፡፡ ይህም ያ ቁርአን (ይከልከሉ፤ ይልቁንም በልቦቻቸው ላይ ይሰሩት የነበሩት (ኃጢአት) ደገደገባቸው፤የተባለው ነው›› ብለዋል፡፡

- ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስም «ፈትናዎች በልቦናዎች ላይ እንደሰሌን ገመዶች አንዳንድ እያሉ በልቦናዎች ላይ ያርፋሉ፡፡ እሺ አሚን ብሎ የተቀበላቸው ልብ ውስጥ ጥቁር ነጥብ ሆነው ይቀመጣሉ፡፡ እንቢ አልቀበልም ባለ ልብ ውስጥ ደግሞ ነጭ ሆነው ይቀመጣሉ፡፡
  በሁለት ልቦች ላይ እስከምትሆን ድረስ፡-
- በነጭ ልብ ላይ እንደ ሶፋ ጋራ ጠንካራ ወይም እንደ ብር ንፁህ በመሆን ምድርና ሰማይ እስካሉ ድረስ በየትኛውም ፈትና ጉዳት ሊደርስበት የማይችል፡፡
- ሌላው አመዳማ ጥቁር እንደ ተዘቀዘቀ (ተገለበጠ) የውሃ ኩባያ ሆኖ ጥሩንና መጥፎን ሳይለይ በስሜቱ የሚሰጠውን ብቻ ተቀባይ እስከሚሆን ድረስ» ብለዋል፡፡

1

- ልባዊ አምልኮቶችን ማወቅ አካላዊ ተግባራትን ከማወቅ የበለጠ በማንም ሰው ላይ ግዴታ ይሆናል፡፡
- ምክንያቱም ልባዊ አምልኮቶች ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ አካላዊ አምልኮቶች ደግሞ የእነሱ ቅርንጫፎች፤ ለእነሱ ሟሟያዎችና የእነርሱ ውጤቶች በመሆናቸው ነው፡፡

- ነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ፡-

‹‹አላህ ወደ አካላችሁም ሆነ ወደ ንብረታችሁ አይመለከትም፡፡ ግና ወደ ልቦቻችሁና ወደ ተግባራችሁ (ስራዎቻችሁን) ይመለከታል›› ብለዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ልብ የእውቀት ማጠራቀሚያ እና የምርምር ማካሄጃ ቦታ ነው።
- ለዚህም ነው በአላህ ዘንድ በሰዎች መካከል ማበላለጥ የሚቻለው በልብ ውስጥ በሰረፀ ኢማንና ኢኽላስ እና እርገጠኝነት መሠረት የሆነው።
- ሀሰኑ-ልበስሪ እንዲህ ይሉ ነበር፡- (በጌታዬ እምላለው አቡበከር ሰዎችን በሰላትም ሆነ በፆም አልቀደማቸውም። አቡበከር ከሰዎች የበለጠው በልቡ ውስጥ በሰረፀው ብርቱ እምነት ብቻ ነው።) ብለዋል።

አፍሪካ አካዳሚ

- የልብ ተግባራት ከአካላት ተግባራት በብዙ ምክንያቶች ይበልጣሉ፡፡

1) የልብ አምልኮ ሲበላሽ የአካልን አምልኮ ያበላሻል፡፡ ምሳሌውም ለይዩልኝ መስራትን ይመስል ነው፡፡

2) የልብ ተግባራት ዋና መሰረት ነው፡፡ በመሆኑም በልብ ሳያስቡት በድንገት የተከሰተ እንቅስቃሴም ሆነ ንግግር በአላህ ዘንድ አያስጠይቅም፡፡

3) የልብ ተግባራት በጀነት ውስጥ ከፍተኛ ማዕረግን የምታስገኝ በመሆኗ ለምሳሌ ዙሁድን ይመስል ነው፡፡